# የትግሬ ቀባሪ

ዘውዲቱ የማነ
2018-05-05

ህዝቡ በአንድ ሆኖ ተከባብሮ ሲኖር

ኢትዮጵያ በሚላት በሚወዳት አገር

እስላም ክርስቲያኑ የኖረው በፍቅር

ክፉ ቀን አታምጣ ብሎ ሲለው ለእግዜር

አጠር አርጎ ነግሮት ብቻውን እንዳይቀር

ቀባሪ አታሳጣኝ ብሎ መማፀኑን ያዘወትር ነበር።

አምላክ የህዝቡን ቃል የፀሎቱን ብሂል

በጥሬው ተርጉሞ ወርቁን ሳይቀላቅል

የትግሬ ቀባሪ የላከ ይመስል

በገባበት ገብቶ በዋለበት ውሎ

አሳዶ አንከራቶ ገርፎና አጎሳቁሎ

ቅጥረኛ አሰማርቶ ከቤቱ አፈናቅሎ

መውጫ መግቢያ ሲያጣ ኑሮውን ሲያማርር

ገሎ ይቀብረዋል ፀሎቱ እንዲሰምር።

https://www.youtube.com/watch?v=glYcPhu6z1c